# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومـــو


Gaafa: 22-08-2012 تاريخ

Lakk.: No.: 014/stm-abo/2012 رقم

## የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን እረፍት በተመለከተ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ

መለስ ዜናዊና ፓርቲው ኢህኣዴግ በውጭ ሃይሎች በተደገፈ የጦር ሃይል ስልጣን የያዙት ከ21 ኣመታት በፊት ነበር። ያለፉት ሃያ ኣንዱ ኣመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ህዝቦች የጦርነት፣ የግጭት፣ የጅምላ ሰብኣዊ መብት ረገጣዎች፣ የእስራት፣ የኣፈና፣ የግድያና የረሃብ ዘመን ነበር።

የመለስ ዜናዊ ማለፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙና ላለፉት 21 ኣመታት ሰብኣዊ መብቶቻቸው በዚህ ኣምባገነንና በተላላኪዎቹ ሲረገጥ ለኖረው ብዙሃን ህዝቦች ኣንፃራዊ እረፍት ሊሆን ይችላል። መለስ ዜናዊ በኢምፓየሪቷ ገዢዎች ታሪክ ውስጥ ከዋነኛና ኣስመሳይ ጨካኝ መሪዎች ኣንዱ ነበር። ኣሁን ስልጣን ለቆ መሄዱ እውነተኛ የዴሞክራሲ ስርኣት በመዘርጋት ከኣንድ ክፍለ ዘመን በላይ የዘለቀውን የኣለመግባባት ችግር በሰላማዊ መንገድ ለማስወገድ እድል ይከፍት ይሆናል።

መለስ ዜናዊ በወንጀልና በጭካኔ በተሞላው የኣገዛዙ ዘመን በቅኝ ግዛትነት ከተያዙት እንደ ኦሮሞ፣ የኦጋዴን ሶማሊ፣ ሲዳማ፣ ኣፋር፣ ጋምቤላና ከሌሎች የኢምፓየሯ የፖለቲካ ማህበረሰቦች በሺዎች የሚቆጠሩትን ዜጎች ኣቁስሏል፣ ገድሏል፣ ኣስሯል፣ በቶርቸር ኣሰቃይቷል፣ ከሃገር እንዲሰደዱ ኣስገዷል። ይህንን ግፍ ኣልቀበልም ብሎ ባመው ትውልድ ላይ እነመለስ ዜናዊ የፈጸሙት በጭካኔ የተሞሉ ወንጀሎች በወንጀሉ ሰለባ ቤተሰቦችና ዘመዶች ዘንድ ለዘላለም የሚረሳ ኣይደለም። ከዚህም በተጨማሪ በዚህ የኣገዛዝ ዘመኑ ሙስና በእጅጉ በመንሰራፋቱ የፖለቲካው፣ የኢኮኖሚውና የወታደራዊው ተቁዋማት ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች በሙሉ ከትግራይ በመጡ ዘመድ ኣዝማዶቹ ተይዘዋል። በዚህ ላይ ደግሞ ከፋፍሎ የመግዛት ፖልሲው ሲታከልበት ቀደም ሲል የነበረውን ስጋትና ምሬት ይበልጡኑ በማባባስ ለተጨማሪ ኣለመግባባቶች መንገድ ጠርጎኣል።

ኣሁን መለስ ዜናዊ ሄዷል። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ህዝቦችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ካሁን ወዲያ ሌላ ኣምባገነን የሃገሪቷን የፖለቲካ ስልጣን ነጥቆ እንደገና እንዳይገዛቸው በከፍተኛ ጥንቃቄ መከላከል የግድ ይላቸዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ በኣንድ ፈላጭ ቆራጭ ኣምባገነናዊ መሪ የሚተዳደር ስርኣት ካሁን በሁዋላ ማክተም ይኖርበታል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ህዝቦች ኣሁን የተፈጠረውን ኣጋጣሚ በመጠቀም እጅ ለእጅ ተያይዘው ለዘመናት የዘለቀውን የፖለቲካ ችግር ከፍፃሜ ለማድረስ የጋራ መፍትሄ እንዲ ያፈላልጉ በዚህም ለልጅ ልጆቻቸውና ባጠቃላይ ለወደፊቱ ትውልድ መልካም የዴሞክራሲ ባህል እንዲያወርሱ ጥሪ እናቀርባለን።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር

ነሃሴ 22, 2012


P. O. Box 6973 Asmara, Eritrea |Tel 2911 153848 | E-mail abamilki@gemel.com.er www.oromoliberationfront.org